# የሚኒስትሮች ም/ቤት ያጸደቀው
# የፀረ-ሽብርተኝነት ሕግ

Wednesday, 03 June 2009 http://www.ethiopianreporter.com/content/view/5515/54/

>የመኪና እና የቤት አከራይ በ 24 ሠዓት ለፖሊስ ማሳወቅ አለበት

>በተጠርጣሪ ቤቶች የተለያዩ የመረጃ መሣሪያዎችን ማስቀመጥ ይፈቅዳል

>ያለ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ስልክ፣ ኢንተርኔትና ፋክስ መጥለፍ ያስችላል

>የአሉ-አሉ ምስክርነት በፍርድ ቤት ተቀባይነት ይኖረዋል

>ፓርላማውአሸባሪ ቡድኖችን ይሰይማል

በጌታቸውንጋቱ

የኢፌዴሪ መንግሥት የሚኒስትሮች ምክር ቤት የፀረ ሽብርተኝነት ረቂቅ አዋጅ አፀደቀ፡፡ ረቂቅ ሕጉ ወደ ሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተመርቷል፡፡

የመንግሥት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት ሚኒስትር ዲኤታ አቶ ኤርምያስ ለገሠ ከትናንት በስቲያ በጽሕፈት ቤታቸውበሰጡት መግለጫእንዳስታወቁት ..ሽብርተኝነት መዋጋት የሕልውና ጉዳይ ነው.. ብለዋል፡፡ ኢትዮጵያ በተለያዩ ጊዜያት የሽብር ጥቃቶች ሰለባ ብትሆንምእስካሁን ድረስ የፀረ ሽብርተኝነት ሕግ ሳይኖራት መቆየቷን የገለፁት ሚኒስትር ዲኤታውበሽብር ጥቃት ውድመት መከሰቱ፣ በልማት ላይ አደጋ በመደቀኑና ሕገ መንግሥታዊ ስርዓቱን ለመጠበቅ ሕጉን ማውጣት እንዳስፈለገ ተናግረዋል፡፡ በኢትዮጵያ እስካሁን ያለው የወንጀል ሕግ ሽብርተኛነትን የማይመለከትና በሥራ ላይ ያሉት ሌሎች የወንጀል ሕጎችም በቂ ባለመሆናቸውየሽብር ጥቃቶችን በብቃት ለመመከት ለሕግ አስከባሪዎችምችግር ሆኖ እንደነበርና አገሪቱን ከሽብር ጥቃት ለመታደግና የሕዝብን ደህንነት ለመጠበቅ ሕጉ እንደሚረዳ ተናግረዋል፡፡

በሚኒስትሮች ምክር ቤት የፀደቀውይህ ረቂቅ አዋጅየአፍሪካን፣ የፀረ ሽብርተኝነት ኮንቬንሽን፣ የሕንድ፣ የዩጋንዳ፣ የደቡብአፍሪካ፣ የካናዳ፣ የእንግሊዝና ሌሎች አገራት ልምድን በመውሰድና የኢትዮጵያን ልምድ በማካተት መቀረፁን አቶ ኤርሚያስ አመልክተዋል፡፡

በረቂቅ አዋጁ ላይ የተከራይ መረጃ የመያዝና የማሳወቅ ግዴታ በሚለው ስር ..ማንኛውም ቤት፣ ቦታ፣ ክፍል ወይም ተሽከርካሪ ወይም ተመሳሳይ መገልገያ አከራይ የሆነ ሰው የተከራዩን ማንነት በዝርዝር እና በፅሁፍ የመያዝና በአቅራቢያው ላለ ፖሊስ ጣቢያ በሃያ አራት ሰዓታት ጊዜ ውስጥ የማሳወቅ ግዴታ አለበት..ይላል፡፡ አቶ ኤርምያስ ይህንን አስመልክተው ሲያብራሩ በግብፁ ፕሬዚዳንት ሆስኒ ሙባረክ ላይ የሽብር ጥቃት የሰነዘሩት ሠዎች ቤትና መኪና ተከራይተው ሲዘጋጁ እንደነበርና ከመኪና አከራይ በወቅቱ ተገኝቶ የነበረው መረጃ ወንጀለኞቹን ለመያዝ ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳበረከተ አስታውሰዋል፡፡

በዚሁ ረቂቅ አዋጅ ላይ የሽብርተኛ ድርጊት ተብለው የተዘረዘሩት ማንኛውም ሰው የፖለቲካ፣ የሃይማኖታዊ፣ ወይም የአይዲዮሎጂ አላማን ሆን ብሎ መንግሥትን በማስገደድ ወይም በማስፈራራት፣ ሕዝብን በማስፈራራት፣ የአገርን የፖለቲካዊ የሕገ መንግሥታዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ወይም ማኅበራዊ ተቋማትን በማናጋትና በማፍረስ፣ ሰውን የገደለ ወይም በአካሉ ላይ ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ፣ የሕዝብን ደህንነትና ጤና ለአደጋ ያጋለጠ፣ እገታ ወይም ጠለፋ የፈፀመ፣ በንብረት ላይ ጉዳት ያደረሰ፣ በተፈጥሮ ሃብት፣ በአካባቢና በታሪካዊ ወይም ባህል ቅርስ ላይ ጉዳት ያደረሰ፣ የሕዝብ አገልግሎትን ለአደጋ ያጋለጠ፣ የያዘ፣ በቁጥጥር ስር ያደረገ፣ ያበላሸ የሚሉት ተካትተዋል፡፡

በሐሰት ስለ ሽብርተኝነት ድርጊት በመናገር ማስፈራራት ስለ ሽብር መረጃ እያለው ለፖሊስ አለመግለፅና በወቅቱ አለማሳወቅም ያስጠይቃል፡፡

የሽብርተኝነት ድርጊትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የብሔራዊ የመረጃና ደህንነት አገልግሎት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘውም በሽብርተኝነት ወንጀል የተጠረጠረ ሰውን የስልክ፣ የፋክስ፣ የሬዲዮ፣ የኢንተርኔት፣ የኤሌክትሮኒክስ፣ የፖስታና የመሳሰሉ ግንኙነቶችን ለመጥለፍ ወይም ለመከታተል፣ ጠለፋውን ለማስፈፀም ወደማናቸውም ቤት ውስጥ በሚስጢር መግባት፣ እነዚህን ለማስቀመጥ የሚረዱ መሣሪያዎችና ለመጠቀም አገልግሎቱን ከሚሰጡ ድርጅቶች አስፈላጊውን ትብብር ማግኘት ይችላል፡፡

በሽብር ወንጀል የተጠረጠረን ሰው የፌዴራል ፖሊስ ያለ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ መያዝ እንዲችል ሕጉ የሚፈቅድ ሲሆን ተጠርጣሪው ከተያዘ በኋላ ለፍርድ ቤት ማሳወቅ እንደሚገባ ይገልፃል፡፡ በሽብር ወንጀል በተጠረጠረ ሰው ላይ ፖሊስ ምርመራውን ለማጣራት የ 28 ቀናት የጊዜ ቀጠሮ እስከ አራት ወራት ድረስ በተከታታይ መጠየቅ እንደሚቻል በረቂቁ ቀርቧል፡፡

ምስክርን በማሰማት ረገድ በፍርድ ቤት የተለያዩ መረጃዎች፣ ሪፖርቶች፣ የዲጂታል መሣሪያዎች፣ የጽሑፍ ማስረጃዎች እንዲሁም የሰሚሰሚ ምስክሮች ተቀባይነት እንደሚኖራቸው ተቀምጧል፡፡ የሰሚሰሚ ምስክር ጥያቄ ቢያስነሳም የተፃፈ ሕግ ያላቸው አገራት፣ ምስክር መቀበል ላይ ዘና ያለ አቋም እንዳላቸውና ዳኛው ምስክሩን ተቀብሎ የራሱን ምዘና እንደሚያደርግ አቶ ሽመልስ ከማል በማብራሪያቸው አመልክተዋል፡፡

አንድን ድርጅት ወይም ቡድን ..ሽብርተኛ.. ብሎ የመሰየም ስልጣን በዚህ ሕግ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የተሰጠ ሲሆን ሽብርተኛ ብሎ የሰየመውን ስያሜ መልሶ የመሻር መብትም የዚሁ ምክር ቤት ነው፡፡ የተለያዩ አገራት አንድን ቡድን አሸባሪ ብሎ የመሰየም ስልጣን ለተለያዩ አካላት የሚሰጡ መሆኑን የገለፁት አቶ ኤርሚያስ ለገሠ በኢትዮጵያ ይህንን ሥራ የሕዝቡ የቀጥታ ተወካዮች ቢሰሩት ይመረጣል ተብሎ ለፓርላማው መሰጠቱን ገልፀዋል፡፡

የሽብርተኛ ድርጊትን ማበረታታት በሚለው በረቂቅ ሕጉ አንቀፅ ስር ማንኛውም ሰው የወንጀል ድርጊት ተብለው የተዘረዘሩትን ድርጊቶች ወይም የሽብርተኛ ድርጅት አላማን የሚያበረታታ፣ የሚደግፍ ወይም የሚያራምድ፣ ቅስቀሳ ወይም መልዕክት የፃፈ፣ ያዘጋጀ፣ ያተመ፣ ያሳተመ፣ ያሰራጨ፣ ያሳየና ያሰማ እንደሆነ በሕግ ተጠያቂ እንደሚያደርገው ይገልፃል፡፡

ከላይ የተጠቀሱትንና ሌሎች ጉዳዮችን የዳሰሰው የፀረ ሽብርተኝነት ረቂቅ ሕግ እስከ ሰኔ ወር መጨረሻ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ፀድቆ የአገሪቱ ሕግ አካል ይሆናል ተብሎ ይጠበቃል፡፡

ኦትዮጵያ በ1995 ዓ.ም. በአዋጅ ቁጥር 301/95 የአሸባሪዎችን የፈንጂ ጥቃት መከላከያ ዓለም አቀፍ ኮንቬንሽን፣ ሽብርተኛነትን ለመከላከል እና ለመዋጋት የአፍሪካ አንድነት ድርጅቶች ኮንቬንሽን (302/95)፤ እገታን መከላከያ አለም አቀፍ ኮንቬንሽን በተመሳሳይ ዓመት ማፅደቋና የራሷ ሕግ አካል ማድረጓ ይታወቃል፡፡